# ጎሰኝነት የሰው ልጅ ጠላት

ጌታቸው ኃይሌ

በየጊዜው የሚታተሙት ዜናዎች ፥ አሳቦችና አስተያየቶች እንደሚያመለክቱት ፥ የኢትዮጵያ በአንድ ሀገርነት መቀጠል ጎሰኝነት አደጋ ላይ እንደጣላት ብዙዎቻችን አምነናል ። ጎሰኝነት እንደ ናዚዝም እና እንደ ፋሺዝም የሰው ልጅ ጠላት ነው ።

<u>ሕዝቡ ይጠየቅ ፤</u>

አደጋው እንዳይደርስ የሚጥሩትም እንዲደርስ የሚገፉፉም ወገኖች ድምፃቸው እኩል ይሰማል ። ሁለቱም ወገኖች "ሕዝቡ ይጠየቅ" እያሉ በሕዝብ ስም ይምላሉ ። መሐላው ቢያንስ ሦስት ጉልሕ ችግሮች አሉት ፤

አንደኛ ፥ ሕዝብ የሚጠየቀው ብዙ ሀገሮችን አንድ ሀገር ለማድረግ እንጂ አንድን ሀገር ብዙ ሀገሮች ለማድረግ አይደለም ። ይኸንን እክል ውድቅ ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎች የሶቪየት አንድነትንና የዩጎዝላቪያን መፈራረስ ፥ የቸኮዝሎቫኪያን ሁለት አገሮች መሆን ለምሳሌነት ይጠቅሳሉ ። ሆኖም እነዚህ ሀገሮች የተከፋፈሉት የፈጠሩት የነፃ ሀገሮች አንድነት አልሠምር ስላለ ነው ። አልሠምር ስላለ ፡ ቀረ ። ኢትዮጵያ ግን ቆዳዋ ሲጠብ ሲሰፋ የኖረች አንድ አገር እንጂ የነፃ ሀገሮች ስብስብ አይደለችም ። የሀገር ገዳዮች ግፊት ወደቀድሞው እንመለስ ሳይሆን ፥ አንድ ፍሬ ስትቀበር ብዙ ፍሬ እንደሚወለድባት ኢትዮጵያን እንቅበርና ብዙ አገሮች እናስወልዳት ነው ። እነዚህ ሰዎች የረሱት አገሮቹ ሲወለዱ የተጠላውን የባህል ጭቆና ይዘው መሆኑን ነው ፤ ማለትም ፥ የአሁኒቱ ኢትዮጵያ እንድትከፋፈል የተፈለገው ከባህል ጭቆና ለመዳን ከሆነ ፥ የባህል ጭቆና የሌለበት አገር አይወለድም ። ልዩነቱ ለያንዳንዱ አዲስ አገር አዲስ ጨቋኝ ማንገሥ ነው ።

ሕዝቡ ይጠየቅ ከተባለ ፥ ኢትዮጵያ የጎሳዎች ስብስብ ነች ከተባለ ፥ ለአንድ ጎሳ  አንድ ድምጽ በመስጠት ይሞከር ። ጎሳ የሚታወቀው በቋንቋው ስለሆነ ፥ ለአማራው አንድ ድምፅ ፡ ለትግሬዩ አንድ ድምፅ ፥ ለኦሮሞው አንድ ድምፅ ፥ ለአርባ ሁለቱ የደቡብ ጎሳዎች አርባ ሁለት ድምፅ ፥ ወዘተ ተፈቅዶለት አማርኛ በኦሮምኛ እንዲተካ ይፈልግ እንደሆን ይጠየቅ ።

<u>ሁለተኛ ፥</u> አገራችንን ለመከፋፈል ብንወስን እንኳ ታማኝ ዘዴና ታማኝ አካፋይ ዳኛ የለም ። እንኳን አገርን ፥ ሁሉም የሚቀበሉት ድምበርንን የሚያዋስን ፥ ምርጫን የሚታዘብ እንዳልተገኘ አይተናል ። ኤርትራን ለመገንጠል የተፈጸመውን ወንጀል መድገም ይሆናል ።

<u>ሦስተኛ ፥</u> ለመከፋፈል መሠረቱ ፥ የክፍሎቹ ብዛት እና ድምበራቸው የሚወሰነው እንዴት ነው? ይኸንን ጥያቄ ቀላል ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎች የሚሰጡት መልስ "ቋንቋን መሠረት ማድረግ ነው" የሚል ነው ። ለምንድነው ቋንቋ መሠረት የሚሆነው? ደግሞስ አንድ ቋንቋ ብቻ የሚነገርበት ክፍል የታለ? አሃ! መልሱ ፥ "ሌሎቹን ማባረር ፥ መግደል ፤ መጨቆን" ሊሆን ነዋ!

***<u>የጥፋተኞችን ወንጀል አናጸድቅም ፤</u>***

***ለክፍፍል የቋንቋን መሠረትነት መቀበል የወያኔዎችንና የኦነጎችን ወንጀል የጽድቅ ሥራ ለማድረግ የሚደረግ ጥረት ነው ። ሁለቱ የአመፅ ድርጅቶች “ኢትዮጵያን በቋንቋ ከፋፈሏት” ይባላል እንጂ ፥ እነሱ ያደረጉት የሚፈልጉትን ግዛት አንሥተው የቀረውን በመሰላቸው መከፋፈል ነው ። ባጭሩ ፥ “በጎሳ መከፋፈል” የሚለው ሐሳብ የተወለደው የእነዚህን የሁለት ድርጅቶች ፍላጎት ለማሟላት ብቻ ነው ። ፍላጎታቸው አንድ ነፃ ትግራይ ፥ አንድ ነፃ ኦሮሚያ ለመፍጠር ነው ። ይኸን የሚክድ ካለ ፥ማስረጃው ቀላል ነው ። አንደኛ ፥ ታሪኩ በዓይን ምስክሮች ተመዝግቧል ። ሁለተኛ ፥ ወያኔዎች ከፈጠሯቸው የጎሳ ድርጅቶች በቀር ፥ እንደ ወያኔና እንደ ኦነግ ራሱን የፈጠረና አዲስ አገር ለመፍጠር የተደራደረ አንድም ድርጅት የለም ። ወያኔዎች የፈጠሯቸውና አሁን የተሰጣቸውን ግዛት የሚገዙ ድርጅቶች በሂደቱ ምንም የተጫወቱት ሚና የለም ። ስለዚህ የፈጣሪያቸውን ቃል “አሜን” ብለው ቢቀበሉ ፥ ለወደፊቱ ሕይወታቸውም “ፈጣሪያችን ፥ አንተ ታውቃለህ ፤ ፈቃድህ ይሁን” እያሉ ቢማፀኑ እንዘንላቸው እንጂ አይግረመን ። የራሳቸው እንጂ የኢትዮጵያ ጥቅም የማይታያቸው ወያኔ አምላኪ ፍጥረቶች ናቸው ።***

***መከፋፈሉ ታሪካዊት ኢትዮጵያን ከመደምሰስ አልፎ በሌላ በብዙ ረገድ ሁላችንንም እንደሚጎዳ የሕፃን ጭንቅላት ከተሸከመ ሰው በቀር ለማንም ግልጽ ነው ። ዓለም ሁሉንም አይቶ አሁን ወደፊት የሚገሠግሠው አንድ አግጣጫ ባለው የአንድነት አውራ ጎዳና ነው ። “አንድነት ከጎረቤት አገር ጋር ከመጋጨት ፥ የንግድ ውል ከመዋዋል ያድናል” ይላሉ ። ምክንያቱም ፥ ዛሬ ዓለም ለብልጽግናና ለምቹ ሕይወት የሚፈልገው የተፈጥሮ ሀብትና ሰፊ ገበያ ነው ። ዓይኑን ከዚያ ላይ የሚያነሣ ከዓይነ ስውር አይሻልም ።***

***<u>የመለያየት ጥቅም ፤</u>***

***“መለያየት ጥቅም አለው” ከተባለ ተጠቃሚዎቹ ኦሮምኛ ተናጋሪዎችና ትግርኛ ተናጋሪዎች ብቻ ናቸው ። ጥቅማቸው ምን እንደሆነ የሚያውቁት እነሱ ብቻ ቢሆኑም ፥ እንደሚሉት ከሆነ ፥ “የባህል ጭቆና አለ ፤ መፍትሔው ፥ መለያየት ነው” ይላሉ ። የጭቆና መዋያ ይለያያል ፤ የኢኮኖሚ ጭቆና ፥ የቋንቋ ጭቆና ፥ የጾታ ጭቆና ፥ የመልክ ጭቆና ፥ ወዘተ አለ ። መፍትሔው ግን አንድ ነው ፤ ዲሞክራሲ ይባላል ። ለባህል ፥ ለጎሳ ፥ ለቋንቋ ጭቆና “መለያየት” የሚሉት ልዩ መፍትሔ ማምጣት ተንኮልና ኋላ ቀርነት ነው ። ተንኮሉ የራስን ቋንቋ የበላይ ለማድረግ ፥ ተጨቋኝ ከመሆን ወደ ጨቋኝነት ለመዛወር የሚደረግ ጥረት መሆኑ ነው ። በቋንቋ ነፃነት ስም ፥ ቋንቋዎችን ለመጨቆን የሚካሄድ ትግል ። ኋላ ቀርነቱ ደግሞ ፥ ራስን ከጎሳ ውጭ አለማየቱ ነው ። ልብ አላልነው ይሆናል እንጂ ፥ የአንድ አገር አንድ ሕዝብ ከጎሳነት ወጥቶ በአንድ ሕዝብነት ያደገና የጎለመሰ ታላቅ ጎሳ ነው ። በዚህ ጎሳ ውስጥ አለመጠቃለል በጎሳ ዓለም ጨንግፎ መቅረት ነው ።***

***<u>ሐሜት ፤</u>***

***መከፋፈልን የሚፈልጉ ወገኖች “ኢትዮጵያ በአንድነቷ ትኑር የሚሉ ኢትዮጵያውያን ቋንቋቸው የበላይ ስለሆነ ፥ የገዥው መደብ ወገኖች ስለሆኑ ነው” በማለት ያሟቸዋል ። አማርኛንም መውቀሳቸው ነው ።***

ደካማ ሐሜትና ወቀሳ ነው ። ብሔራዊው ቋንቋ ኦሮምኛ ቢሆን ኦሮሞዎች የኢትዮጵያን መከፋፈል አይፈልጉም ነበር ማለት ነው ። ትግሉ የዲሞክራሲ ሳይሆን የበላይነት ጥያቄ ነው ያልኩት ስለዚህ ነው ። ታዲያ ለምን ስለዲሞክራሲ ያወራሉ? ሰው ለማወናበድ? እንዴት ሆኖ በምንስ ምክንያት አማርኛን በኦሮምኛ እንተካ? ሁለተኛስ እውነት አማርኛ ተናጋሪዎች ብቻ ናቸው የኢትዮጵያን አንድነት የሚፈልጉ?

<u>ማስጠንቀቂያ ፤</u>

ብዙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ፥ ለሀገራቸው ካላቸው ከፍተኛ ፍቅር የተነሣ ፥ "አገር እንገነጥላለን" የሚሉ ድርጅቶች የ "አንገነጥልም" ምልክት ሲያሳዩ እውነት ይመስላቸዋል ። አሁንም ፥ አሁንም ፥ ባል መጣልሽ ሲሏት ፥ "ካልታዘልኩ አላምንም" እንዳለችዋ ቆንጆ ፥ ጎሰኝነትንና የጎሳ ፌዴሬሽንን በይፋ ካላወገዙና ዲሞክራሲያዊ ትግላቸውን "አንድ ኢትዮጵያ ፥ አንድ ሕዝብ ፥ አንድ ሀገር ፥ አንድ ድምጽ ለአንድ ሰው ፥ አንድ ላዕላይ ባንዲራ" ብለው ከሚታገሉ ድርጅቶች ጋራ ካላስተባበሩ ፥ ሌላው ሁሉ አዲስ አገሮች ለመውለድ የሚሰጥ ማወናበጃ ሽንገላ ስለሆነ ፥ አገር ወዳዶች የሆናችሁ የእንግዴ ልጅ አዋላጅ ከመሆን እንድትድኑ አሳብ አቀርባለሁ ። መወለዱ የማይቀር ከሆነ ከጥረቱ ላይ እጃችሁን አጽዱ ፤ በራሱ ይወለድ ። "ጎሰኝነት የማይቀር ነው" ከሚሉ አገር ወዳድ መሳዮች ጋር አትተባበሩ ። እኛ ከተባበርን ይቀራል ። በኃይል የተዘራ እንክርዳድን ማስወገድ የሚቻለው በጉጉት ሳይሆን ፥ ለማረም ታጥቆ በመነሣት ነው ።